# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ሰኔ አንድ - ጥቅምት ሃያ ሁለት

## ሰማዕቶቻችንን እንዴት እንዘከራቸው?

ሕዝባችን ለግንቦት ድሎቹና ለመብቶቹ መከበር ባደረገውና በሚያደርገው ትግል በተለያዩ ጊዚያት ሕይወታቸው በግፍ የተቀጠፈውን፥ አካለ ጎደሎ የሆኑነትን፥ በእስር ቤት እየተሰቃዩ ያሉትን፥ ከቀያቸው የተፈናቀሉትንና የተለያዩ በደሎች የደረሰባቸውን ቆራጥ ዜጎቻችንን ዛሬ የምንዘክራቸው በመሪር ሃዘንና በታላቅ አክብሮት ነው።

በግንቦት ፺፯ ምርጫ ሕዝባችን አንደኛ በነቂስ ወጥቶ ተሳትፎ በማድረጉ፥ ሁለተኛ የሕወሓት//ኢሕአዴግን መሪዎች በምንም ዓይነት በማያወላዳ ሁኔታ በዝረራ በማሸነፉ፥ ሦስተኛ ደግሞ ይኽንን ድሌን በጠራራ ፀሐይ አልነጠቅም ብሎ ከነዚህ ጥቂቶች ጋር እልህ በተጋባ መልክ ትንንቅ በመቀጠሉ፤ በፖለቲካ ያገባናል ለሚሉ ኃይሎች በማስተላለፍ ላይ ያለው መልእክት ለማንኛችንም ምንም ምርጫ የተወ አይመስልም። ሕዝባችን ለገዥው ሥርዓት አራማጆችም ሆነ ለሕዝቡ ወገኖች ያቀረበላቸው ምርጫዎች ግልጽ ናቸው።

ለኢሕአዴግ መሪዎች የሰጠው ምርጫ ሽንፈትን በፀጋ ተቀብሎ በቀረበላቸው የብሔራዊ እርቅ አሳብ መስማማት ወይም ደግሞ በለየለት ሽብር በመሰማራት አገር ለመግዛት መሞከር የሚል ነው። እነዚህ ከግል ጥቅም በስተቀር ለአገርና ለወገን ቅንጣት ታህል መቆርቀር የማያሳዩ እራስ-ወዳድ ግለሰቦች ግን ይኽንን ሁለተኛውን አካሄድ መርጠው ተጨማሪ ዴሞክራሲ ቀርቶ ቅድመ-ምርጫ ሲመፃደቁበት የቆዩበትን የይስሙላ ዴሞክራሲ የፍንጭ ፍንጭ እንኳን ለማረጋገጥ ተስኗቸው አገራችንን፥ ሕዝባችንንና እራሳቸውንም ጭምር ወደ ጥፋት ይዘው እየነጎዱ መሆናቸው ግልጽ ይመስለናል።

ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችም ያቀረበላቸው አማራጭ <u>ድምፄ ይከበር</u> የሚለውን ዓቢይ ጥሪ (አጀንዳ) ሳይሸራረፍ ተቀብለው የትግሉ ባለቤት ለሆኑት ሚሊዮኖች አመራር ሰጥተው ለድል ማብቃት ወይም ደግሞ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለሚደረገው የሽግግር ሂደት አስፈላጊ የሆነውን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) ቀልብሶ፥ ለሽብር አገዛዝ ተንበርክኮ፥ ሕዝብን አውላላ ሜዳ ላይ በትኖና አጋፍጦ ከታሪክ መድረክ መውረድ ነው። ይኽ እንዲሆን መፍቀድ ደግሞ የዴሞክራሲው ሂደት ተጋድሎ ምናልባት ለአንድ ትውልድ የሚተላለፍበትና የወያኔ/ኢሕአዴግ አጥፊ ማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች መርኃ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) መረን ተለቀው አገራችን እንደ አገር፥ ሕዝባችን እንደ ሰብኣዊ ፍጡር ኅልውናቸው ከባድ ፈተና ላይ የሚወድቅበት ዘግናኝ ሁኔታ እንዲሰፍን የሚያደርግ አካሄድን መከተል ነው የሚሆነው። ይኽንን ሁለተኛውን አማራጭ ኅብረታችን እንኳን ሊመርጠው ሊያስበውም ይቀፈዋል።

በኢዴኃኅ (በኅብረታችን) እምነት ዛሬ ሕዝባችን የተያያዘው ትግል ከኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች፥ ከሠራዊቱ፥ ከፖሊሱና ከደኅንነቱ ጋር ሳይሆን እፍኝ ከማይሞሉ ሙሰኞችና ፀረ-ሕዝብ ከሆኑት አንጋቾቻቸውና ተባባሪዎቻቸው ጋር የተያዘ የሞት የሽረት ፍልሚያ ነው። ይኽንን ጥቂቶች በኢትዮጵያችን ላይ ለመጫን የሚፍጨረጨሩትን የጥፋት ጉዞ ለመግታት እንዳስፈላጊነቱ በይፋም ሆነ በህቡዕ በተደራጀ ሕዝባዊ ትግል በቁርጠኝነት ከመቀጠልና ከድል በመለስ ሌላ አማራጭም ተስፋም አይኖርም። ከዚህም ተነስተን በአረመኔዎች እጅ የወደቁ ሰማዕት ወገኖቻችንን ዛሬ ስንዘክር የዚች አገር እጣ ፈንታ ጉዳይ


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ያገባናል ለሚሉ ወገኖች ሁሉ ሦስት ቁም-ነገሮች ላይ ያተኮረ መልእክት ለማስተላለፍ እንፈልጋለን።

## 1. ትግሉን እንቀጥል ካልን ... ሕዝባዊ አጀንዳ!

አጀንዳችን አፈናንና ሽብርን እየተቃወመና እየተቋቋመ እዛው በዛው ደግሞ ትግሉ በሕዝባዊ ድል እልባት የሚያገኝበትን የድምፅ መከበርንም ስትራቴጅያዊ ጥያቄ ያነገበ ጥንድ አጀንዳ መሆን ይኖርበታል። ሁለቱ የሚተጋገዙ እንጂ የሚነባጠሉ አይደሉም።

የሕዝባዊው አጀንዳ መጀመሪያ ገጽታው ዛሬ ደብዛቸው እየጠፋ ባሉት መሠረታዊ መብቶች ዙሪያ መንቀሳቀስ የሚል ነው። ይኸ አጀንዳ "በግፍ የታሰሩ ዜጎች ይፈቱ" ፥ "የነፃው ፕረስ ባልደረቦች ተለቀው ያለአንዳች ጫናና ተፅዕኖ የሕዝብ ድምፅ መሆናቸውን ይቀጥሉ" በሚሉ መደበኛ ሊባሉ በሚችሉ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የሚወሰን አይደለም። ከነዚህ እኩል "ዝቅተኛ"ና መሠረታዊ ብለን በምንገምታቸው "የኢሕአዴግ መንግሥት ያሰራቸውን በይፋ አሰርኩ ይበል፥ ዝርዝራቸውን ለዘመድ ወዳጅ ይፋ ያውጣ፥ የታሰሩበትን ቦታ ለቤተዘመድ ያሳውቅ፥ የጅምላ መቃብሮች ተከፍተው ወላጅ እርም ያውጣ፥ በግፍ የተገደሉ ዜጎችም በሥነ-ሥርዓት ይቀበሩ፥ ተጠያቂነት ይኑር፥ ከግንቦት ጀምሮ ስለተፈጸመው ግፍ ዓለም-አቀፍ ልዩ አጣሪ አካል (ኮሚሽን) ይቋቋም" በሚሉት የሚሊዮኖች እንባ በሚፈስባቸው አንገብጋቢና አጣዳፊ ጥያቄዎች ዙሪያ ተንቀሳቅሰን ሕዝባችንን ማንቀሳቀስም ይኖርብናል።

የሕዝባዊው አጀንዳ ሁለተኛ ገጽታ የሕዝቡ ድምፅ ይከበር የሚለው ጥያቄ ነው። በአሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ እንደሚታየው ይኸ መሠረታዊ የሕዝብ አጀንዳ "ለጊዜው" ወደ ጎን ተገፍቶ ትግሉ መሠረታዊ መብቶች ይከበሩ፥ የታሠሩት ይፈቱ በሚሉት መፈክሮች ዙሪያ ብቻ እንዲያተኩር ጥረት እየተደረገ ይመስላል። ለዚያውም ደግሞ ይኸንን እንኳ ይባስ ተብሎ በሕዝባችን ተጋድሎ ሳይሆን "በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ ትግል" እውን ለማድረግ የሚሞከርና የቅልበሳውን አደጋ በጣም ዝቅ አድርጎ የሚገምት አዝማሚያ እናያለን። የአገሪቱ ዴሞክራቶች በሙሉ ከፍ ብለን በጠቆምናቸው አንገብጋቢና አጣዳፊ ጥያቄዎች ዙሪያ መታገላቸው ተገቢ ብቻ ሳይሆን ቁልፍና አስፈላጊም ነው። ነገር ግን ለዚህ ዓላማ ተገቢ ቦታ ሰጥቶ የሚካሄደው ትግል ለአንድ አፍታም ቢሆን <u>የሕዝብ ድምፅ</u> ይከበር የሚለውን መፈክራችንን ሊያስረሳን አይገባም እንላለን። ከእንግዲህ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች <u>በሕዝብ ትግል የሚነጠቅ ማንኛውም ድል በሕዝብ ድምፅ መከበር እስካልተቋጠረ ድረስ ምንም ዓይነት ዘላቂነት አይኖረውም።</u> <u>ፀረ-ሕዝቦቹ በሕዝባዊ ትግል እስካልተንበረከኩ ድረስ ከእጃቸው የተፈለቀቀውን ማንኛውንም ድል ጊዜና አጋጣሚ ጠብቀው መልሰው ሊቀሙን የሚችሉበት፥ በትግል የተፈቱት እስረኞቻችን መልሰው የሚታሰሩበት ወይም በሌሎች የሚተኩበት እንዲሁም በትግል የተመለሱት መሠረታዊ መብቶቻችን ተመልሰው የሚነጠቁበት ሁኔታ ይከሰትና ነገሩ ሁሉ ታጥቦ ጭቃ ይሆናል ማለት ነው።</u>

## 2. ሕዝባዊ አጀንዳ ካልን ... ሕዝባዊ ትግል!

ሕዝባችን ድምፁን ለማስከበር አጀንዳውን አንግቦ በመንቀሳቀስ ላይ በመሆኑ የሕዝብ ወገኖች ነን የምንል ይኸንን አጀንዳ አንግበን እንደባለቀው ካልን የትግሉ ባለቤት ራሱ ሕዝባችን እንደሆነ መቀበላችን የግድ ይሆናል። በእኛ እምነት ይኸ የትግሉ ሕዝባዊ ገጽታ በሌላ የትግል መልክ ሊተካ አይችልም። ትጥቁን ይፍታና እኛ በሰከነ ፓርላሜንታዊ ትግል ወይም ደግሞ በዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ እገዛ ተደራድረን ነፃ ፕረሱንም እናስመልሳለን፥ የፖለቲካ እስረኞችን እናስፈታለን፥ የዳኝነት ነፃነት የሚረጋገጥበትም ሁኔታ እናመቻቻለን፥ ለቀጣዩ ምርጫ ነፃ የምርጫ ቦርድ እናቋቁማለን ብሎ ማሰብ እየታገለና እየተሰዋ ጣፊያ ለተነሳ ሕዝብ በጥቂቶች ጥረት ታላቅና ታናሽ ይቀርብለታል (ይሰጠዋል) እንደማለት ያህል አጓጉል አካሄድ ነው። ቧልት ነው። ይኸ አባባላችን ለሃቀኛ ድርድር መቆም እንጂ ድርድርን መቃወም ማለት አይደለም። ሃቀኛ ድርድር ደግሞ የማይታለፉ ቅድመ ሁኔታዎች አሉት።

አንደኛ ደጋግመን እንዳልነው ማንኛውም ድርድር የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በሕዝብ ተገድዶ የሚቀበለውና ኅብረተሰቡም በተጠንቀቅ ቆሞ የሚከታተለውና የሚያጅበው ሂደት መሆን ይኖርበታል።
ሁለተኛ የዚህ ድርድር ዐቢይ አጀንዳ የሕዝብ ድምፅ ይከበር የሚል መሆን ይኖርበታል።
ሦስተኛ ፍሬያማና ውጤታማ ድርድር ማድረግ የሚቻለው ለእስር የተዳረጉት መሪዎችና ሌሎች ዴሞክራቶች ነፃ ወጥተው ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች፥ የሲቪክ ማኅበረሰብ፥ የገበሬዎች፥ የሠራተኞች፥ የነጋዴዎች፥ የሴቶች፥ የተማሪዎች፥ የወጣቶችና የሌሎች የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች በሚሳተፉበት ሁሉን-አቀፍ አገራዊ መድረክ አማካኝነት የሚደረግ እንጂ በመደራደር ስም ጥቂቶች ከጥቂቶች የሚመሳጠሩበት ሂደት መሆን አይችልም። ይኽን ሁሉ እውን ለማድረግ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በቅድሚያ ከተያያዙት የሽብር ጎዳና በሕዝብ ትግል እንዲያፈገፍጉ መደረግ ይኖርባቸዋል። ለዚህ ደግሞ የሕዝባችን ተጋድሎ ተአማሚነት ያለው ከፖለቲካ ድርጅቶች የሰፋ ሕዝባዊ አመራር ያስፈልገዋል።

## 3. ሕዝባዊ ትግል ካልን... ሕዝባዊ አመራር!

ዛሬ ደከምና ፈዘዝ ብሎ የሚያየው ሕዝባዊ ትግል ከግንቦት በኋላ በተላያዩ ምክንያቶች የተከሰተውን የአመራር ክፍተት ተቋቁሞ ለበርካታ ወራት ከሞላ ጎደል በግብታዊነት የተካሄደ በተለይም ደግሞ በአገራችን ወጣቶች ደም፥ በወላጆች እንባና መከራ የተፃፈ አኩሪ የትግል ምዕራፍ አስመዝግቧል። በእነዚህ ወራት የሕዝብ ቁጣና የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ትንኮሳ እየተጋገዙ የቀሰቀሷቸውና ብዙ መስዋእትነት የተከፈለባቸው ሰላማዊ ሰልፎች፥ ሥራ ማቆም አድማዎችና ሌሎች ግብታዊ ተጋድሎዎች ተመዝግበዋል። ትግሉ ከእንዲህ ዓይነቱ ግብታዊነት ወጥቶ የፖለቲካ አመራርና ቅንብር የሚያገኝበት ዘዴ በአስቸኳይ ካልተበጀለት አገራችን የሚጠብቃት ችግርና አደጋ መሆኑ ግልጽ ከሆነ ውሎ አድሯል። አንደኛ ፍሬው የማይታይ መስዋእትነት ከፍተኛ ጉዳት ከማምጣቱም በላይ መሰለቻት ሊጋብዝ ይችላል። ትግሉ በጠንካራ አመራር ያልተደራጀ ያልተቀናጀና ያልተመራ እስከሆነ ድረስ ይዋል ይደር እንጂ የተደራጀው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ኃይል ሊያከሽፈው ይችላል። ከዚህ አጣብቂኝ ውስጥ መውጣት የሚቻለው ሕዝባዊ ትግሉ ሕዝባዊ አመራር ሲያገኝ ብቻ ነው።

የግንቦት ትግል ተአማኒ የሆነ አንድ ወጥ አመራር አግኝቶ ይፋፋም ስንል ዛሬ ለዚህ አጀንዳ የቆሙ ወገኖች በሙሉ ለጊዜው ምንም አይነት የድርጅት አጥር ሳይወስናቸው በውጭም በውስጥም <u>" ዜጎች ለግንቦት ድሎች "</u> በምትል ወሳኝ መፈክር ዙሪያ በአንድነት ይነሱ ማለታችን እንደሆነ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ አውስተናል። ይኽንን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ በአንድ በኩል ከፖለቲካ ድርጅቶች፥ ከድጋፍ አካሎች፥ ከሴቶች፥ ከወጣቶችና ከሌሎች የሲቪክ ማኅበረሰብ ስብስቦች፥ ከታዋቂ ኢትዮጵያውያንና የአገር ሽማግሌዎች የተውጣጣ <u>የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል</u> ተቋቁሞ በውጭ አገር አንድ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ እንዲጠራ ተደጋጋሚ ጥሪ አድርገናል።
በተደጋጋሚ ያደረግነው ጥሪ በአንድ በኩል የምናካሂደው ትግል ከጊዜም ጋር እንደሆነ ባልገባቸው ዳተኞች፥ በሌላ በኩል ደግሞ ዘግናኝ በሆነ ጠባብ ድርጅታዊ ስሌት ራሳቸውን አጥረው በተቀመጡ ጥቂቶች፥ ወይም ደግሞ አንድ አገር አድን ሃሳብ ሲቀርብ በቀረበው ሃሳብ ላይ ሳይሆን ሃሳቡን በአነሳው ላይ በሚያተኩሩ ተጠራጣሪዎች መሰናክልነት እስካሁን ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል። ይኸም ለሕወሓት/ኢሕአዴግ ቀልባሾች የሕይወት እስትንፋስና ፋታ እየሰጠ አገራችን መመለሻ ወደሌለው የጥፋት አዘቅት እንድታመራ እያደረገ ነው።
ዛሬ የግንቦቱን የሕዝብ ድል አስመልሶ በእነሱ ላይ ለመገንባት እያታገለ ያለውና በሰፊና ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ የጋራ ትግሉ ተአማኒ አመራርና አዲስ እመርታ እንስጠው ከሚለው በሚሊዮን ከሚቆጠረው ሕዝብ አንፃር እነዚህ ኃይሎች እዚህ ግባ የሚባል ክብደትም ሆነ ጫና ያላቸው አይደሉም። እኛ ለአገራችን አንድ ቁም ነገር እንሥራ የምንል ኃይሎች ሕዝባዊ አጀንዳ፥ ሕዝባዊ ትግልና ተአማኒነት ያለው አመራር የሚለውን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ ከልብ ከተንቀሳቀስን ሕዝባችን ድል እንዲቀዳጅ ከማድረግ የሚያግደን ምንም ኃይል ሊኖር አይችልም።

ዛሬ የሰኔም ሆነ የጥቅምት ሰማዕቶቻችንን ለመዘከር በምንነሳበት ወቅት በእነዚህ ሰማዕቶቻችንና ዛሬ በእስር በሚማቅቁት የፖለቲካ መሪዎቻችን፥ በነፃው ፕረስ ባልደረቦች፥ በሲቪኩ ማኅበረሰብ መሪዎችና በሽህ የሚቆጠሩ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ፊት <u>"ትግሉ ይቀጥላል"</u> ብለን ስንነሳ ይኸን የሰማዕታት ቀን የዛሬ ዓመት ደግሞ እንደገና በሃዘን ለማስታወስ ቀነ ቀጠሮ በሚይዝ መንፈስ መሆን የለበትም፡፡ የአቶ መለስ ዜናዊ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ የሽብር አገዛዝ የሚቀጥለው ዓመት የግፉን ሁለተኛ፥ በቀጣዩ ዓመት ደግሞ ሦስተኛውን፥ በቀጣዩ ደግሞ አራተኛውን በጥልቅ አዘን እየዘከርን እንቀጥላለን የሚለው የተዛባ አስተሳሰብ ከወዲሁ እጅ የሰጠና የሰማዕታትን ደም ከበሬታ የሚነካ አካሄድ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ የእነዚህን ሰማዕታት ተጋድሎ ይበልጥ አቀነባብሮና ጥራት ያለው አቅጣጫ ሰጥቶ ይኸነን አገዛዝ በሕዝባዊ ትግል በማንበርከክ ሰኔም ሆነ ጥቅምት በእነዚህ ሰማዕቶቻችን ደም ኢትዮጵያችን የተጎናጸፈችውን ድል በኩራት የምናከብርባቸው ዕለታት እንዲሆኑ መታገልን እንደ ተቀደሰ አገራዊ ግብና አደራ ወስዶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

በቅርቡ በጥቂት ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ተነድፎ ይፋ የሆነው " የዜጎች ቻርተር ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በመሰራጨት ላይ ያለው ሰነድ በበጎ አሳቢ አገር-ወዳድ ወገኖች ከሚደረጉ አዎንታዊ ጥረቶች መካከል ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ ኢዴኃኅ ሰነዱን በጥሞና መርምሮና ተወያይቶበት ሰነዱ ዘርፈ ብዙ ለሆኑ የአገራችን ችግሮች መፍትሔ በማስገኘት በኩል እጅግ ጠቃሚና ዐቢይ አስተዋጽ የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ ለአሳቡ አነሳሾች አዎንታዊና አበረታች መልእክት አስተላልፏል፡፡ አሁን የሚቀረው ተጎታችነትን አስወግዶ በአስቸኳይ አንድ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ በመጥራት የጉባዔው ተሳታፊዎች በዚህ ሰነድ ላይ አሳብ በመስጠትና በማዳበር ሆነ ሌሎች ያለተጠቀሱ ጉዳዮችን በማንሳት ሰፋ ያለ ውይይት አድርገው መግባባትና ስምምነት ላይ እንዲደርሱና ከስምምነቱ አንድ የጋራ ሰነድ  እንዲፈልቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው እንላለን፡፡ በዚሁ ጉባዔ ላይ የግንቦትን ድሎች ከሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች መልሶ ለመንጠቅ ስለሚያስፈልገው የጋራ ትግል መዋቅር ጉዳይ ስምምነት ላይ መድረስና ውሳኔ አድርጎ መንቀሳቃስ ለሕዝባችን ትግል አዲስ እመርታ በመስጠት በኩል ወሳኝ ነው፡፡

ኅብረታችን ከዚህ አቋሙ በመነሳት የቻርተሩ አመንጪዎችም ሆኑ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ስብሰቦች፥ ወዘተ... በአስቸኳይ ተገናኝተው ስለዚህ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ የመወያያ ነጥብ/ቦች (አጀንዳ)፥ ስለተሳታፊዎች፥ ስለስብሰባው ቦታና ቀን ተጨባጭ ዝርዝር ውሳኔዎች ለማድረግ ሳይውሉ ሳያድሩ አንድ አዘጋጅ ኮሚቴ እንዲሰይሙ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡ ይኸንን አገራዊ ህልማችንን እውን ለማድረግ " ሁሉም እስኪስማማ" እንጠብቅ ከተባለ እስከዛሬ ተሞክሮ ባልሰራውና የአገራችንን እጣ ፈንታ ለዳተኞችም ሆነ ለጠባብ ቡድነኞች በሚያስረክበው አደጎኛ ጎዳና መኳተን እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱን ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ እውን ለማድረግ የጊዜውን አጣዳፊነት ተገንዝበው ለመንቀሳቀስ በሚፈልጉ ኃይሎች ወስኖ ማካሄድ አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው ብለን የምናምን መሆኑን ስንገልጽ ለተግባራዊነቱ አሁንም ጉዳዮ ለሚለመለከታቸው ሁሉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

የሰማዕቶቻችንን ኅያውነት የምናረጋግጠው እነሱ የወደቁበትን ዓላማ እውን ለማድረግ በጋራ መቆም ስንችል ብቻ ነውና በመቻቻል የጋራ ትግሉን ማጎልበት የማንኛውም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገን ሃላፊነት ይሆናል፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.